# 3ኛ ዮሐንስ (22)

## (3ኛ ዮሐንስ 1-8)

የጥናት ዓላማ፡ ስለወንድሞቻችንና እህቶቻችን የምናሰራጨው ዜና ሰሚውን የሚጠግን እንጂ የሚያረክስና የሚያፈርስ ሐሜት የሞላበት እንዳይሆን እንድንጠነቀቅ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹ለእውነት ታማኝ እንደሆንህና የምትመላለሰውም በእውነት እንደሆነ አንዳንድ ወንድሞች መጥተው ስለ አንተ ሲመሰክሩልኝ…› 3ኛ ዮሐ 3

1. 3ኛ ዮሐ 1-8 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ3ኛ ዮሐንስና በ2ኛ ዮሐንስ መልዕክት አጀማመር መሃል ምን ተመሳሳይነት ይታይሃል;
2. አማኝ ሁሉ በሙሉ ጤንነት ሊመላለስ ይገባዋል የሚለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ቁ2 ትን እንደማረጋገጫ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ለምንድነው በአንተ አመለካከት ይህ ክፍል ለዚህ አይነቱ ትምህርት ማረጋገጫነት ሊጠቀስ የማይችለው;
3. በቁ3 ላይ የተጠቀሱት ወንድሞች ስለ ጋይዮስ ያመጡት መልዕክት ምን ነበረ; ጋይዮስ ስህተት ሳይኖርበት ቀርቶ ወይስ ሰዎቹ የሚያወሩትን የመምረጣቸው ጉዳይ ነው ብለህ ትገምታለህ; አንተስ ሰለሰዎች የምታመጣው ሪፖርት ምን ዓይነት ይሆን;
4. ሐዋርያው ስለ ጋይዮስ የሰማውን መልሶ ለጋይዮስ መንገር ለምን አስፈለገው; ከዮሐንስ ድርጊት ምን መማር እንችላለን;
5. በ2ኛ ዮሐንስ ቁ4 ትና በ3ኛ ዮሐንስ ቁ4 የምታየው ተመሳሳይነት ምንድነው; 2ኛ ዮሐ ቁ4 ‹በእውነት ጸንተው እየሄዱ› 3ኛ ዮሐ ቁ4 ‹በእውነት የሚመላለሱ› የሚሉት ሃሳቦች የሚጠቁሙን ሃሳብ ምንድነው;
6. በ2ኛ ዮሐ ቁ10 እና በ3ኛ ዮሐ ቁ5 መካከል ቅራኔ ታያለህ ወይ; መልስህን አስረዳ፡፡
7. ቁ6 ‹እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ብትረዳቸው…› ይህ እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኝ የተባለው ነገር የሚጠቀልለው ምን ምንን ሊሆን ይችላል ብለህ ታምናለህ;
8. ቁ8 ትን በማንበብ ለወንጌል እውነት አብሮ መስራት ካስፈለገ ማድረግ ከሚገቡን ነገሮች አንደኛው ምንድነው ይላል;
9. ስለ ጋይዮስ ዜናን ያመጡት ወንድሞች የዮሐንስን ልብ በደስታ ሞላ፡፡ አንተስ ስለወንድሞችህና እህቶችህ የምታሰራጨው ዜና ልብን የሚሰብር ነው ወይስ የሚጠግን;